# የ2017 በጀት ዘመን የስራ ማስኬጃ በጀት—
# ለወደፊታችን ገንዘብ ለማቅረብ የታጥቀን እንስራ ጥሪ

ለወደፊት የተማሪ ስኬት ጠንካራ መሰረት መገንባት እና የግኝት ክፍተትን ለመዝጋት የሙአለንዋይ ፈሰስ ማድረግ—ያ ነው በትምህርት ቦርድ የ2017 በ. ዘ. የስራ ማስኬጃ በጀት ጥያቄ የሚገፋው ስልት። የተጠየቀው የ2017 በ. ዘ. የስራ ማስኬጃ በጀት 2,500 ተጨማሪ ተማሪዎች ለማገልገል የሚያስፈልጉ መገልገያዎች፣ የግኝትን ክፍተት ለመዝጋት፣ የተማሪዎችን መሰረተ ትምህርትና የሂሳብ ክሂሎቶች ለማሻሻል፣ የክፍል ተማሪዎችን ቁጥር ብዛት ለመቀነስ፣ የሰራተኞችን ባህላዊ ችሎታ ለመገንባት፣ ተማሪዎችን ለመደገፍ ከማህበረሰቡና ከቤተሰቦች ጋር ይበልጥ ጠንካራ ሽርክናዎች ማሳደግ፣ የሰራስተኛ ሀይልን ለማሻሻልና አይነት ለማስፋፋት/diversify ጥረቶችን ማፋጠን፣ እና እያንዳንዱ ተማሪ ለኮሌጅና ለስራ ዝግጁ መሆኑን ለማረጋገጥ ዲስትሪክቱን በተሻለ ለማደራጀት አላማ ያላቸው የሙአለንዋይ ፈስሶች ማድረግን ያጠቃልላል።

የተጠየቀው በጀት የተመሰረተው ባለፉት ስምንት አመቶች ለበጀት የተካሄደው የገንዘብ አቀራረብን መለወጥ አስፈላጊነቱን መሰረት በማድረግ ነው። ከ2009 ጀምሮ፣ ለበጀት ገንዘብ የቀረበው ለእንክብካቤ ጥረት ደረጃ እጅጉን በጣም ያነሰውን ወይም ከዚያ በታች በሚገኝ ገንዘብ መጠን ነው። ይህ የክፍል ተማሪ ቁጥር ብዛት መጨመር፣ በተፈላጊ ሙያዊ እድገት ላይ ማነሰን አስከትሏል፣ እና ተማሪዎች ስኬታማ ለመሆን የሚያስፈልጓቸው ድጋፎችና ጣልቃገብነቶች ያነሱ እንዲሆኑ አድርጓል። ለት/ቤቶቻችን የሚያስፈልጋቸውን የሙአለንዋይ ፈሰስ ደረጃ በሙሉ ለማግኘት ጊዜ ይወስዳል፣ ቢሆንም ለወደፊቱ መሰርቱን ማጠናከር መጀመር እና በ2017 ብ. ዘ. ስልታዊ የሙአለንዋይ ፈሰሶች ማድረግ አለብን። መቆየት አንችልም።

## ለተማሪዎቻችን የወደፊት ስኬት ለመገንባት ወደፊታችንን ገንዘብ እንድናቀርብለት ይገባናል።

ለወደፊት ገንዘብ ለማቅረብ የመጀመርያ እርምጃ በማደግ ላይ ለሚገኘው የተማሪዎች ቁጥር ተመሳሳይ ደረጃ አገልግሎቶች ለማቅረብ የበቂ ሃብቶች መኖር ነው። ከዚያም፣ የግኝትን ክፍተት የሚያጠቡ ስልቶችን መደገፍ ያስፈልገናል። በዚያው መጠን፣ በየእለቱ ልጆቻችንን በሚያገለግሉ አስደናቂ ሴቶችና ወንዶች ላይ ሙአለንዋይ ማፍሰስ አለብን። ከዚያም እያንዳንዱን ድርጅት የሚገጥመው የግሽበትና የሌሎች ዋጋ ጭማሪዎች አሉ። እነዚህን የዋጋ ጭማሪዎች ባነሰ ደረጃ ለመጠበቅ ቅልጥፍናዎችን በየመስኩ ፈልጎ ለማግኘት MCPS እጅግ ከመጠን በላይ የሆኑ ጥረቶች አድርጓል። በተጨማሪ፣ ይህ በጀት የዲስትሪክቱን መሰረት ከMCPS ስልታዊ ተቀዳሚዎች ጋር ቅንብር ለማጠናከር ግብ ላላቸው ብልፅግናዎች ገንዘብ የሚያቀርብ $5.8 ሚልዮን ቁጠባዎችንና ቅነሳዎችን ያካትታል።

ባጠቃላይ፣ ቦርዱ የተቀበለው በጀት የሚያካትተው፡-

| | |
|---|---|
| የምዝገባ እድገት/አዳዲስ ት/ቤቶች እና ተጨማሪ ቦታ | $22.4 ሚልዮን |
| ግሽበት፣ የዋጋ ለውጦች፣ እና ሌሎች ጭማሪዎች | 1.5 ሚልዮን |
| ለወቅቱ ሰራተኞች/ጡረተኞች የጥቅማጥቅሞች ዋጋ ጭማሪዎች | 26.4 ሚልዮን |
| የድርድር ስምምነቶች ለሰራተኛ ደሞዝ ጭማሪዎች | 55.3 ሚልዮን |
| ስልታዊ ብልፅግናዎች (ገፅ 2 ተመልከቱ) | 48.6 ሚልዮን |
| ቁጠባዎች | –5.8 ሚልዮን |
| የበጀት ጭማሪ | $148.4 ሚልዮን |

የቦርዱ በጀት ጥያቄ የMontgomery County ምክር ቤትን በተጨማሪ የሚጠይቀው በ2016 በ. ዘ. ጥቅም ላይ የዋለውን የ$24 ሚልዮን የአንድ ጊዜ ገንዘብ ወጪ እና ከስቴት ወደ ካውንቲ የተዛወሩትን የአስተማሪ ጡረታ ወጭዎች ለመክፈል የተደረጉ ተጨማሪ $7.9 ሚልዮን እንዲተካ ነው። ከነዚህ ሁለት ጉዳዮች ጋር የበጀቱ ጭማሪ $180.3 ሚልዮን—7.8 በመቶ ይሆናል።

ይቀጥላል

ስልታዊ ብልፅግናዎች

የትምህርት ቦርድ በማሳሰብ ላይ የሚገኘው $48.6 ሚሊዮን አላማ በተደረገባቸው፣ የተማሪን ግኝት ለማሻሻልና የግኝትን ክፍተት ለመዝጋት ስልታዊ ብልፅግናዎች ላይ ነው። ሁሉም ብልፅግናዎች ከዲስትሪክቱ የትግባሬ ፕላን እና ከስድስት ስልታዊ ተቀዳሚ የትኩረት መስኮች (ፍትህና ባህላዊ ችሎታ፤ መሰረተ ትምህርትና ሂሳብ፤ ለስራ ዝግጁነት፤ ሽርክናዎችና ተሳትፎ፤ ተጠያቂነትና ውጤቶች፤ እና ሰብአዊ ካፒታል አስተዳደር) ጋር የተቀናጁ ናቸው። ብልፅግናዎቹ እጅጉን ለላቁ ብቃትና ውጤታማነት ለአዲሶችና ለተስተካከሉ ሁለቱንም ያካትታሉ።

### ቁልፍ ብልፅግናዎች የሚያካትቱት፡-

- የክፍል ተማሪዎች ቁጥር ብዛት 2009 ወደ ነበረው ደረጃዎች መመለስ
- የግኝትን ክፍተት ጥያቄ ለመወጣት ከፍተኛ ተፅእኖ ባላቸው ት/ቤቶች ተጨማሪ የትኩረት መምህራን ማቅረብ
- ሂሳብንና መሰረተ ትምህርትን ለመደገፍ የባለሙያ እድገትን መጨመር
- የስራ አማራጭ መንገዶችን ማበልፀግ እና በፕሮግራም ምዝገባን ማሳደግ
- ለአፍሪካን አሜሪካን፣ ላቲኖ፣ እና በኤኮኖሚ ለተጠቁ ተማሪዎች የግኝት ክፍተትን ለመዝጋት በአካዴሚያዊ ፕሮግራሞች ሙአለንዋይ ፈሰስ ማድረግ።
- ሙአለህፃናትን ማስፋፋት
- የአማካሪዎች፣ ሳይኮሎጂስቶች፣ እና የፒውፕል ፔርሶኔል ሰራተኞች ቁጥር መጨመር
- ለት/ቤቶች የበለጠ ጥንቁቅ ድጋፍ ለማቅረብ የፍትህ ባለሙያዎችን ቁጥር መጨመር
- የወላጅ ማህበረሰብ አስተባባሪዎች መጨመር
- በኢሌሜንታሪ ደረጃ የቤት ት/ቤት ልዩ ትምህርት ማስፋፋት
- የኮሌጅ/ስራ ዝግጁነት ለማረጋገጥ ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ኮርሶች/ተሞክሮዎች መተግበር
- የሰራተኛ ሃይል ለመሻሻልና አይነት ለመጨመር ጥረቶችን ማፋጠን
- በChildren’s Opportunity Fund አማካይነት የሰመር ት/ቤት ፕሮግራሞችን ማስፋፋት
- የተማሪ ውጤቶችን ለማሻሻል የግምገማ ስልትን ማበልፀግ
- ለኤሌሜንታሪ የሂሳብ መምህራን ተጨማሪ ድጋፍ መስጠት
- ባለሁለት ቋንቋ ፕሮግራሞችን ማበልፀግ



0871.16 • EGPS • 1500